# የሽያጭ የጨረታ ማስታወቂያ
## የተለያዩ የቴሌኮም ኔትወርክ ዕቃዎችን ለመሸጥ
## ጨረታው የሚቆይበት ጊዜ፡- ከመጋቢት 10 እስከ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም
## የጨረታ ቁጥር፡- 12/2010

ኢትዮ ቴሌኮም የተለያዩ የቴሌኮም ኔትወርክ ዕቃዎችን ባሉበት ሁኔታ ለህጋዊ ድርጅቶች በጨረታ አወዳድሮ ለመሸጥ ይፈልጋል፡፡ ተጫራቾች የጨረታ ሰነድ ለመግዛት በሚመጡበት ወቅት የዘመኑ ግብር የተከፈለበትን የታደሰ የንግድ ፈቃድ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት፣የታደሰ መታወቂያ ወይም ማንነታቸውን የሚገልፅ ማስረጃ ዋናውንና ኮፒ ይዘው መቅረብ ይኖርባቸዋል::

1. ተጫራቾች ዝርዝር መግለጫ የያዘውን የጨረታ ሰነድ ከመጋቢት 10 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም ዘወትር በሥራ ሰዓት ከሰኞ እስከ ዓርብ ከዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 214 የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል መውሰድ ይችላሉ፡፡
2. ተጫራቾች ለሽያጭ የቀረበዉን የተለያዩ የቴሌኮም ኔትወርክ ዕቃዎችን የጨረታ ሰነዱን የገዙበትን ደረሰኝና ማንነታቸዉን የሚገልጽ መታወቂያ መያዝ አቃቂ በሚገኘዉ የኢትዮ ቴሌኮም ዕቃ ግ/ቤት (AW2) በመገኘት ከመጋቢት 10 ቀን 2010 ዓ.ም. እስከ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ድረስ ማየት ይችላሉ፡፡
3. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ ውጤቱ እንደታወቀ የሚመለስ የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለመግዛት የሚያቀርቡትን ዕቃዎች ጠቅላላ ዋጋ 5% (አምስት ከመቶ) ማስያዝ ይኖርባቸዋል፡፡
4. የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትናዉ ከታወቀ ባንክ ተረጋግጦ በሚቀርብ ሲፒኦ (CPO) መሆን አለበት ፡፡
5. ተጫራቾች የተለያዩ የቴሎኮም ኔትወርክ ዕቃዎችን የሚገዙበትን ዋጋ በተዘጋጀው የዋጋ ማቅረቢያ ቅጽ/ፎርም መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ተጫራቾች መግዛት የሚፈልጉትን የተለያዩ የቴሌኮም ኔትወርክ ዕቃዎችን የሚያሳይ የዋጋ ማስገቢያ ቅጽ/ፎርም፣ የታደሰ የንግድ ፈቃድ ኮፒ፡ የተጨማሪ እሴት ታክስ ምዝገባ ሰርተፊኬት ኮፒ፤የጨረታ ማስከበሪያ ሲፒኦ (CPO)፣ የተጫራቾች አድራሻ መግለጫን በማካተት በታሸገ ኤንቨሎፕ ሙሉ አድራሻውንና የጨረታውን ቁጥር በመጥቀስ በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 214 ከመጋቢት 10 ቀን 2010 ዓ.ም እስከ መጋቢት 24 ቀን 2010 ዓ.ም. ከቀኑ 10፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡
6. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው መ/ቤት ቢሮ ቁጥር 213 መጋቢት 25 ቀን 2010 ዓ.ም ከጥዋቱ በ4፡00 ሰዓት ይከፈታል፡፡ ሆኖም በመክፈቻው ቀንና ቦታ ተጫራቹ ወይም ሕጋዊ ወኪሉ ካልተገኙ እንደተገኙ ተቆጥሮ በተገኙት ተጫራቾች ፊት ያቀረበው ሠነድ ይከፈታል፡፡
7. ኢትዮ ቴሌኮም የተሻለ ዘዴ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
8. ለተጨማሪ መረጃ መስቀል ፍላወር ሆቴል ፊት ለፊት በሚገኘው በኢትዮ ቴሌኮም ዋናው ዕቃ ግምጃ ቤት ሥራ አስኪያጅ ቢሮ በግንባር በመቅረብ ወይም በስልክ ቁጥር 0114653894 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡